በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ጥር 27 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

# 14ኛ አስቸኳይ የካቢኔ ስብሰባ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት ጥር 27 ቀን 2011 ባካሄደው 14ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. የኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፤ መንግስት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማሻሻል የቴሌኮሙኒኬሽን የገበያ ስርአቱን እንደገና ለማደራጀትና በውድድር ላይ የተመሰረተ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር የወሰነ በመሆኑ፤ መንግስት የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያውን እንደገና ለማዋቀርና በቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድርን ለማስፈን ያስቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማሳካ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋም አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የገንዘብ ሚኒስቴር ስለ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኂላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
2. በመጨረሻ ም/ቤቱ የተወያየው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት ለማጽደቅ በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን ስምምነቱ ለአገራችን የሚያስገኘውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ም/ቤቱ ረቂቅ አዋጁ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//